EthioLion

# ለአንድ ኅብረተሰብ ዕድገትና ብልፅግና ወሳኝ የሚሆኑ መሠረተዊ ነገሮች

ዶር ኤረንነ ቀልብሰው (ሐምሌ 2002 ዓ/ም)
(ekelbisow@yahoo.com)

አንድ ኅብረተሰብ አድጎና በልጽጎ እንዲገኝ የሁሉም ዜጋ፥ ኗሪና የእውነተኛ ወዳጅ ፍላጎትና ምኞት እንደሚሆን አይጠረጠርም። ነገር ግን የአንድ ኅብረተሰብ ዕድገትና ብልፅግና ራዕይ ባለቸውና በእውነት ለሁሉም ጥቅም በሚቆሙ መሪዎች አማካይነት በሚጣል መልካምና ጠንካራ መሠረት ላይ በቅንነት በሚሠራ ሥራ ብቻ እንጂ፥ በምኞትና ፍላጎት ወይም አዘውትሮ ስለዚያ ነገር በማውራት፥ ውጤተ-አልባ ሆነው ጊዜን በሚያባክኑ ስብሰባዎች በመሳተፍና ሌሎችን በማሳተፍ፥ እንዲሁም በመፈክሮች ጋጋታ የሚደረሱ ግቦች እንዳልሆኑ ከሌላ ኅብረተሰብም ይሁን ከራሳችን ኅብረተሰብ ከወታደራዊ መንግሥት አስተዳደር ጊዜ ልምድ የምናስታውሰውና ብዙ ማስረጃዎች የሚጠቁሙት ሐቅ ነው። ስለዚህ ለሚያስፈልገን ዓይነት ዕድገትና ብልፅግና መልካም ምሳሌ ሊሆኑ ከሚችሉ ሌሎች ኅብረተሰቦች በመቅሰምና ከታሪክ በመማር (በማስተዋል) ለራስ ሊጠቅም የምችለውን የዕድገት ዘርፍና ተዛማጅ የሆኑ ዘዴዎችን ከአሠራር ስልቶቻቸው ጋር በመምረጥ፥ ከሌላ ቦታ አምጥቶ እንዳለ ለማስቀመጥ በመሞከር እራስን ለውድቀት ከመጋበዝ፥ ለአካባቢው በሚመች ሁኔታ በማሻሻል፥ ቀስ በቀስ ተግባር ላይ ማዋል እንደሚቻል በቅድሚያ መረዳት ተገቢና አስፈላጊ ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

ላንዳንድ ግለሰቦች እንደሚመስልና በመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነገር የእሥራኤል ልጆች ከግብፅ ባርነት እየሸሹ በምድረ ባዳ በነበሩ ጊዜ ከሰማይ መና ወረደላቸው እንደተባለ፥ ዕድገትና ብልፅግና ባንድ ሌሊት እንደጤዛ ወርደው ጧት የሚገኙ እንዳልሆኑ ማንም የሚረደው ይመስላል። በሌላ አገላለጽ ደግሞ፥ ዕድገትና ብልፅግና ከሌላ ቦታ ታሽጎ እንደሚመጣ ዘመናዊ ሸቀጥ ወይም የደብዳቤ ፖስታ በቀላሉ የሚገኙና የሚረከቡአቸው አለመሆናቸውን መረዳት ለማንም የሚከብድ አይመስለኝም። በዚህ አጋጣሚ አሻሚ በማይሆን ግንዛቤ ላይ መደረስ ያለበት ነገር ቢኖር፥ ዕድገትና ብልፅግና በምንም ዓይነት መለኮታዊ ምስጥር እንዳልሆኑ ሁሉም ጠንቅቆ እንዲረደው ያስፈልጋል። ስለዚህ ያለውና የማያወላውል አማራጭ፥ የሰው ልጅ ከፈጣሪው የተሰጠውን የማሰብ ችሎታውን፥ ከትምህርት የሚያገኘውን ዕውቀትና ከሥራ ያከበተውን ልምድ በመጠቀም፥ አንዱ ለሌላው የሚኖራውን ገንቢ ያልሆነ አመለካከት ወይም አስተያየት ወደ መልካም ለውጦና ጠባዩን አስተካክሎ፥ እርስ በርስ በመተማመን፥ በመቻቻልና በመግባባት፥ ለጋራ ጥቅም አቅዶ፥ በቆራጥነት በተግባር ላይ ካዋለ፥ ዕድገትና ብልፅግና በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መድረስ የሚቻል ግብ እንደሆኑ አስቀድሞ መረዳት ያሻል።

Ethiolion.com

EthioLion


# ለአንድ ኅብረተሰብ ዕድገትና ብልፅግና ወሳኝ የሚሆኑ መሠረተዊ ነገሮች

ማንኛውንም የግንባታ ሥራ ሒደት በማጤን የተመለከተ ሁሉ እንደሚረዳና “የሮማ ከተማ ባንድ ቀን አልተገነበችም” እንደሚባል፥ አንድ ኅብረተሰብ ልማትንና ብልፅግናን የራሱ ለማድረግ የሚፈልግ ከሆነ፥ መልካም ዕቅድ አውጥቶ፥ በዘፍጥረት መጽሐፍ ለአዳም “አፈር ነህና ወዳፈር እስኪትመለስ በወዝህ ብላ!” እንደተባለ፥ ለብዙ ጊዜ ልፋትና እንዲሁም ትዕግሥት ለሚያስጨርስ ዓይነት ከባድ ሥራ እራሱን አዘጋጅቶ ሲያያዝ ውጤቱ አስደሳች እንደሚሆን መረዳትና ለሌላ ማስረዳት አስፈላጊ ይሆናል። ከዚህም ጋር በማያያዝ ኅብረተሰቡ ዓላማውን እንዳይስት በየጊዜ እራሱን ማረምና ማስተካከል አስፈላጊ እንደሆነ መረዳት ተገቢ ይመስላል። ኅብረተሰቡ ካሰበበት ለመድረስ የሚችለው ተገቢ የሆነውን ሥራ ቢታክተውም ሳያቋርጥ በመያያዝ እንደሆነ መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ይሆናል። በዚህም አኳያ፥ ኅብረተሰቡ ለዕድገትና ብልፅግና ከሚያደርገው ትግል ጎን ለጎን የሚቀጥለውን ትውልድ ልዩ ትኩረት በመስጠት እያዘጋጀ ኑሮ ከመቀጠል በስተቀር የሚሻል ሌላ አማራጭ አይኖረውም።

የሚመለከተው ኅብረተሰብ በመሪዎቹ አማካይነት እራሱን በራሱ ለመቻል ለሚያደርገው ጥረት ሁሉ ከድርጅቶችም ይሁን ከወዳጅ መንግሥታት አስፈላጊ የሚመስለውን ዕርዳታ ወይም ብድር በሚጠይቅና በሚቀበል ጊዜ በዕኩልነት ላይ ተመሥርቶ በመደራደር ካልሆነ በስተቀር፥ ዞር ብሎ የኅብረተሰቡን ልዕልናንና ማንነቱን በሚነካ ሁኔታ አንደችም ስምምነት ላይ ላለመድረስ ብዙ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ይሆናል። ስለዚህ የራስንና የሚቀጥለውን ትውልድ ልዕልናና ማንነት በማስከበር ከደሀነትና ኋለ ቀርነት ለመላቀቅ የሚቻለው ዛሬ ለነገ ተብሎ ዘለቄታ የሚኖረው ዓይነት ሥራ ሲሰራ፥ ኅብረተሰብ ሲያድግና ሲበለፅግ ብቻ እንደሆነ ግልጽ ነው። ስለዚህ ዘላቂና ሥር የሰደደ ልማትና ብልፅግና ተጨባጭ መሆን የሚችለው ተባብሮና በርትቶ በመሥራት ብቻ እንደሆነ አምኖ መቀበል አመራጭ አይኖረውም።

ስለዚህ “ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ” እንደሚባል፥ ልማትና ብልጽግና ባገር በቀል በሆኑ ባለሙያዎች፥ የሐሳብ ልዩነትን በውይይት በመፍታት፥ በችኮላና በስሜታዊነት ሳይሆን፥ ብዙ ጥናትና ምርምር ታክሎበት፥ በቅንነት ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ እንዲችል ታስቦ የታቀደ፥ ሰፊውን ሕዝብ የሚያሳትፍና አገሬው በቆራጥነትና ጠንካራ መንፈስ በመያያዝ ሊያመጣቸው የሚችል የሥራ ውጤቶች ክምችት እንደሆኑ የሚታመን ነው። የምርቱ ተጠቃሚ የሚሆን ሁሉ በመተባበር፥ እርስ በርስ በመከባበር፥ በመደማመጥ፥ በመወያየትና በመስማማት፥

EthioLion



# ለአንድ ኅብረተሰብ ዕድገትና ብልፅግና ወሳኝ የሚሆኑ መሠረተዊ ነገሮች

በየሙያውና እንዳቅሙ፥ በያለበት አስፈላጊውን መስዋዕትነት መክፈልና ድርሻውን የማበርከት ግዴታ የሚኖርበት ይመስላል። በኅብረተሰቡ ቀጣይነት ለሚኖረው ልማትና ዕድገት ከታሰበ፥ ለተሳታፊዎቹ ሁሉ ደህንነት፥ አስተማማኝና ዘለቄታ ያለ ሰላም መኖር ተገቢ እንደሆነ በመረዳት፥ እንዲሁም ሌሎች አመቺ የሆኑ ሁኔታዎችን መፍጠርና ማዘጋጀት አማራጭ የማይኖረው የኅብረተሰቡ መሪዎች ትክክለኛ የሥራ ድርሻ ቢሆንም፥ በፈቀደኛነት የሁሉም ዜጋ ተሳትፎ አስፈላጊ እንደሆነ ከማንም የተሰወረ ምስጥር አይመስልም።

በማያያዝም ላንድ ኅብረተሰብ ዕድገትና ብልጽግና የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች ምን ይመስላሉ ቢባል፥ እንደ ኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃና እንደ ታዛቢው አመለካከት ሊለያዩ እንደሚችሉ ግልጽ ይመስላል። ስለዚህ በዚህ ጸሓፊ አመለካከት ዕድገትንና ብልፅግናን ለረጅም ዘመናት ለተራቡና ለተጠሙ ሁሉ፥ ለኢትዮጵያና ሌሎች ተመሳሳይ ኅብረተሰቦች ጭምር፥ በዕድገት መምጠቅ እንዲችሉ ወሳኝ ናቸው ተብለው የተገመቱና የተመረጡ ስድስት መሠረተዊ ጽንሰ ሐሳቦች ይኖረሉ። በእያንዳንዱ ወሳኝ መሠረታዊ ሐሳብ ላይ ልዩ ሐተታ ተዘጋጅቶ በተለያየ ጊዜ ለንባብ ከሚቀርበው፥ ጸሓፊው አንባቢዎችን የሚጠይቅ ነገር ቢኖር የሚቀርቡትን ሐሳቦች መርምረውና ጨምቀው ጠቀሜታ እንዳለው የሚገምቱትን ሐሳብ ወይም ጥርቅም ሐሳቦች፥ አስፈላጊ ከመሰለም አስተካክለው፥ ባሉበት ኅብረተሰብ ወይም ድርጅት፥ በሚጠቅም መልኩ ሥራ ላይ ለማዋል እንዲሞክሩ የታሰበ ነው። የስድስቱ መሠረታዊ ሐሳቦች ዝርዝር የሚያካትተው 1) መልካም አመራር መኖር፥ 2) ሰብዓዊ መብት መከበር፥ 3) መሠረታዊ ፍላጎቶች መሟላት፥ 4) የሥራ ዕድል መኖር፥ 5) ቀልጣፋና ሚዛናዊ አገልግሎት መስጠትና መቀበል መቻል፥ 6) ወጣቱን ጥራት ባለ ትምህርትና ሙያ እንዲሁም በመልካም ሥነ ምግባር ማነጽና ማዘጋጀት ይሆናል።

በመጨራሻም ያንድ ኅብረተሰብ የልማትና ብልፅግና ዘመቻ ትክክለኛ መስመር እንደያዘ የሚታወቀው ወሳኝ በሆኑ መሠረታዊ ነገሮች የተጠቆሙ ዓይነት ሐሳቦች በበርካታ ቦታዎችና መሥሪያ ቤቶች ተደጋግመው ተግባር ላይ በመዋላቸው የሚታየው ውጤትና የውጤቱ ከምችቶች የሚኖረውን ሕዝብ፥ ተገልጋይና ተመልካች ጭምር የሚያረኩ ሆኖው ሲገኙና ሌላውን ደግሞ ለማስቀናት ወይም ለተሳትፎ የመሳብ ብቃት ሲኖረቸው ብቻ ነው። ስለዚህ በሚቀጥለው ጊዜ ከላይ በተመለከተው ርዕስ ሥር **"መልካም አመራር መኖር"** በሚለው በመጀመሪያ መሠረታዊ ሐሳብ ላይ የሚቀርበውን ሐተታ እንዲያነቡ በአክብሮት ተጋብዘዋል።

ዶር ኤረንነ ቀልብሰው (ሐምሌ 2002 ዓ/ም)
(ekelbisow@yahoo.com)

EthioLion.com